# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ሰመጉ

## 145ኛ ልዩ መግለጫ

# በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን በወልዲያ እና አካባቢው የተፈፀመ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት

ነሐሴ 03 ቀን 2010 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ
አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19
ስልክ: (+251) 011 558-2387
ፋክስ: (+251) 011 551-7704
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com info@ehrco.org
ድረ ገጽ: www.ehrco.org
ፌስቡክ፡ https://www.facebook.com/humanrights.council.5?ref=bookmarks
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ
ስልክ: (+251) 011 558-2387
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com /monitoring@ehrco.org

ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

| | |
|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 660-2664፣ ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | አዲስ አበባ ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432 |

## ማውጫ


1. ኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ... 4

2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ... 5

3. መግቢያ ... 6

4. የልዩ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች ... 7

4.1. የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ ... 7

4.2. ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ ... 7

4.3. በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ ... 7

4.4. የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ... 8

4.5. የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ... 8

5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች ... 8


5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ) ... 8

5.2 የአካል ጉዳት ... 13

6. ማጠቃለያ ... 18

7. ማሳሰቢያ ... 19

# 1. ኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

---

[1] ኢትዮጵያ [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት፣ ሰመጉ ላለፉት 26 ዓመታት ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፤ በማከናወንም ላይ ይገኛል። የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል። በተጨማሪም ሰመጉ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ያሠራጫል፤ የአድቮኬሲ ሥራዎችንም ያከናውናል፤ በነዚህም በፖሊሲዎችና በአፈጻጸማቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር ይጥራል።

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል። ከሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ ማረሚያ ቤቶችንና የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሂደት በመከታተል ፍትሐዊነታቸውንና በአጠቃላይም የዳኝነት ነጻነት መኖሩን መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከነዚህ በተጓዳኝ ሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና አቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ ተግቶ በመሥራት ላይ ይገኛል።

# 3. መግቢያ

ሰሜን ወሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን በዞኑም ውስጥ 15 ወረዳዎች ይገኛሉ። የሰሜን ወሎ ዞን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች እና ከትግራይ እንዲሁም ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጋር በተለያዩ አካባቢዎች ይዋሰናል።

ሰመጉ በተለያዩ ጊዜዎች በተለይም ባለፉት ሶስት አመታት በአማራ ክልል ህዝቡ የዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ባደረገው እንቅስቃሴ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል። እንዲሁም ከወልቃይት ሕዝብ የማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አጣርቶ ውጤቱን በ141ኛ ልዩ መግለጫው ግንቦት ወር 2008 ዓ.ም ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

አሁንም ከጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተፈጠረው ተቃውሞና የተቃውሞ ሰልፍ ለበርካታ ሰዎች ህይወት መጥፋት፣ መቁሰል፣ መታሰርና ለከፍተኛ የንብረት መውደም ምክንያት ሆኗል።

የግጭቱ መነሻ የሆነው በወልዲያ ከተማ ህዳር 24 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማና በመቀሌ ከተማ መካከል የተደረገውን የእግር ኳስ ውድድር ለመታደም የመቀሌ ከተማ ቡድን ወደ ወልዲያ ከተማ ሲመጣ በየመንገዱ በሚገኙ የተለያዩ ከተማዎች ብሔርን መሰረት ያደረገ ስድብ ይሰማ እነደነበረ በምርመራ ወቅት ያነጋገርናቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ለሰመጉ ገልጸዋል። በረብሻው ምክንያት የእግር ኳስ ጨዋታው እንዲሰረዝ ተደርጎ የመቀሌ ከተማ ቡድን ወደ መቀሌ ሲመለስ መንገድ ላይ በተፈጠረ ግጭት አንድ የመቀሌ ከተማ ቡድን ደጋፊ እንደተገደለ፣ በዚህም ምክንያት ውጥረቱ እየተባባሰ መምጣቱን ጉዳዩን የተከታተሉ የወልዲያ ከተማ ነዋሪዎች ለሰመጉ መርማሪዎች ገልጸዋል።

ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በኦርቶዶክስ ክርስትያኖች ዘንድ በሚከበረው የቃና ዘገሊላ በዓል እለት ፅላት አጅበው ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን ቅጽር ግቢ በሚሄዱ ወጣቶች ላይ የታጠቁ የመንግስት ኃይሎች የአስለቃሽ ጭስ በመወርወራቸው ጽላቱ እስከመውደቅ ደርሷል፤ በዚህም ምክንያት ግጭት ተፈጥሮ ሰዎች ተገድለዋል፣ ቆስለዋል። ይህን ተከትሎ ሕዝቡ በመቆጣቱ በግለሰቦችና በመንግስት ንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል። በዚህ መነሻነት በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎችና ከተሞች ማለትም በቆቦ፣ በሮቢት፣ በመርሳ፣ በውርጌሳ እና በመሳሰሉ አካባቢዎች ዜጎች  ወልድያ ላይ የተፈጸመውን ግድያ በማውገዝ በተለያዩ ቀናት ሰላማዊ ሰልፍ በሚያደርጉበት ወቅት በተነሳ ሁከት ሰዎች ተገድለዋል፣ ቆስለዋል፣ ታስረዋል፣ ከፍተኛ ግምት ያለው የመንግስትና የግለሰቦች ንብረት ወድሟል።

የአካባቢው ህብረተሰብ፣ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦችናየአይን እማኞች ለሰመጉ እንደገለጹት የግጭቱ መነሻ ከላይ የተመለከተው ይሁን እንጂ፣ የተከማቹና ተደራራቢ የሆኑ ችግሮችም ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ይገልጻሉ። እነዚህም

- ሰላም፣ ፍትህ እና የብሔሮ እኩልነት አለመኖሩ፣
- የስራ አጥነትና የስደት መብዛት፣
- የአካባቢው ወጣት በዩኒቨርስቲ ደረጃ ጨርሶ ስራ-አጥ ሲሆን ከሌላ ክልል የመጡትን እንዲቀጠሩ ማድረግ፣
- የድንበር ክልል ጉዳይ መፍትሄ አለማግኘቱ እና
- ከሌላ ክልል መጥተው በማህበር እየተደራጁ የተለያዩ ቦታዎችና ስራዎች ሲሰጣቸው፣ ለአካባቢው ተወላጅ ወጣቶች ይህ እድል መነፈጉ ዋና ዋና የችግሩ መንስኤዎች መሆናቸውን የሰመጉ መርማሪዎች ተዘዋውረው ያነጋገሯቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል።

# 4. የልዩ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች

## 4.1. የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ

ቀደም ብሎ ከላይ እንደተመለከተው ሰመጉ፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች በተካሄዱ የህዝብ ተቃውሞዎች የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጣራት በተለያዩ አካባቢዎች በመገኘት የመስክ ምርመራ አከናውኑዋል፡፡ የዚህ ልዩ መግለጫ አቢይ አላማ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ መፍትሄ እንዲሰጣቸው፣ ጥሰቶች እንዲቆሙና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከል እርምጃ እንዲወስድ ለማሳሰብ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ እንዲሰጣቸውና ድርጊቱን የፈጸሙና ያስፈጸሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁ፣ ጥሰት ፈጽሞ ሳይጠየቁ መቅረት እንዲቆምና ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ የማይፈጸሙበት የፖሊሲና የአሰራር ማስተካከያዎችና እርማቶች ከወዲሁ እንዲደረጉ መጠየቅና መጎትጎት ነው፡፡

## 4.2. ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ

በዚህ ልዩ መግለጫ ውስጥ ይፋ የተደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዓይነትና ዘርፍ ለመረዳትና ለማሳየት በዋና መሠረትነት የሚያገለግሉት፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት፣ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ግዴታም የገባችባቸው የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ናቸው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በየዘርፋቸው በተገለጹበት ቦታ ሁሉ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በመነሻነትና በማመሳከሪያነት ተጠቅሰዋል፡፡

## 4.3. በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ

ይህ 145ኛ ልዩ መግለጫ የሚመለከተው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነው፡፡ የመብት ጥሰቱ የተፈጸመው ከሕዳር 24 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 04 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ ሲሆን ሰመጉ ባለሙያዎቹን ወደ አካባቢው ልኮ የማጣራት ሥራውን የሰራው ከየካቲት 05 እስከ የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ሰመጉ ለዚህ መግለጫ የበቁ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ያካሄደባቸው ወረዳዎች ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ዞኖችና ወረዳዎች

| ተ.ቁ | የክልሉ ስም | ዞን | ወረዳ/ ከተማ |
|---|---|---|---|
| 1 | አማራ ክልል | ሰሜን ወሎ | ወልዲያ ከተማ |
| | | | ወልዲያ ዙሪያ ወረዳ |
| | | | ቆቦ |
| | | | ሮቢት |
| | | | መርሳ |
| | | | ውርጌሳ |
| | | ደቡብ ወሎ | ደሴ |

## 4.4. የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ይህንን ምርመራ በሚያካሄድበት ወቅት ግኝቶቹን ለማረጋገጥና ለማጠናከር በቀጥታ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች አቤቱታና ማስረጃ ተቀብሏል፤ ከምስክሮች የምስክርነት ቃል፣ ድርጊቱ በተፈፀመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ሁኔታውን በዓይን በማየትና በማጥናት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎችም በመረዳት፣ በተጨማሪም የሠነድ፣ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ማስረጃዎችን በመቀበል እና በመመርመር ለመሰብሰብ ተችሏል። እንዲሁም በተቻለበት ጊዜና ስፍራ ሁሉ ከመንግስት አካላት መረጃና ማስረጃ ተሰባስቧል።

## 4.5. የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) አሁን የሚገኝበት በጣም ውሱን የሆነ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የምርመራ ቁሳቁስ አቅም፣ ቀውሶቹ በሚጠይቁት ፍጥነት፣ መጠን፣ ስፋትና ድግግሞሽ ለመስራት አላስቻለውም። በሌሎችም አካባቢዎችና ሁኔታዎች ላይ እንደሚታየው ሁሉ እዚህም ተጎጂዎችና ቤተሰቦች እንዲሁም ምስክሮች በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ መሆንና በሚፈለገው መጠን ትብብር አለማድረጋቸው በዚህ የምርመራ ስራ ሂደት ወቅት ትልቅ ተግዳሮት ፈጥሯል። በመሆኑም የቀሩ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ወደፊት ሰፊና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ እንዲቻል ሰመጉ ተጎጂዎችና ዜጎችን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉለት በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይጠይቃል።

# 5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች

## 5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል። የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል። ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። ኢትዮጵያም እነዚህን አለም ዓቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።

ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ከተሞች ነዋሪ በነበሩ ዜጎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል።

1. **ሟች መምህር ታምሩ በሪሁን፡-** ዕድሜ 42፣ ህዳር 24 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ የወልዲያ ከተማና የመቀሌ ከተማን የእግር ኳስ ጨዋታ ለማየት ቢሄድም ጨዋታው በመሰረዙ ምክንያት ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ ወልዲያ ከተማ በተለምዶ ጎንደር በር ተብሎ በሚጠራው ቦታ ላይ በጥይት በፌደራል ፖሊስ ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉንና በነጋታው ህዳር 25 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ በ8 ሰዓት ወልዲያ ከተማ መድሐኔዓለም ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል።



ሟች መምህር ታምሩ በሪሁን

2. **ሟች ተማሪ ዮሴፍ እሸቱ፡-** ዕድሜ 15፣ ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ላይ የሚካኤል ታቦት በማስገባት ላይ እንዳለ ወልዲያ ከተማ በተለምዶ ሚካኤል ማርገጃ የሚባል ቦታ ላይ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች በጥይት ተመትቶ በባጃጅ ወደ ሆስፒታል በመወሰድ ላይ እንዳለ በድጋሜ በአድማ በታኞች በጥይት በመመታቱ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡ ጥር 13 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡30 ወልዲያ ከተማ ካቴድራል ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ሟች ተማሪ ዮሴፍ እሸቱ

3. **ሟች ገብረመስቀል ጌታቸው፡-** ዕድሜ 35፣ ስራ ነጋዴ የነበረ ሲሆን ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ላይ የሚካኤል ታቦት በማስገባት ላይ እንዳለ ወልዲያ ከተማ መብራት ሃይል መናኸሪያ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ ጥር 13 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡30 ወልዲያ ከተማ ካቴድራል ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል፡፡ በተማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ሟች ገብረመስቀል ጌታቸው

4. **ሟች ወ/ሮ ዝይን ንጋቴ፡-** ዕድሜ 60፣ ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ የሚካኤል ጸበል ተጠርተው ሲመለሱ በመከላከያ ሰራዊት አባላት ጭንቅላታቸው ላይ በጥይት ተመተው ሕይወታቸው አልፏል። ጥር 13 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ በ7 ሰዓት ወልዲያ ከተማ መቻሬ አቦ ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓታቸው ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል። በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል።



ሟች ወ/ሮ ዝይን ንጋቴ

5. **ሟች ንጉሴ አበበ፡-** ዕድሜ 18፣ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ላይ ቆቦ ከተማ የበፊቱ መናኸሪያ አካባቢ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ግራ ጎኑ ላይ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። በእለቱ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ቆቦ ከተማ ጠዘጠዛ ባለ እግዚአብሔር ካቴድራል ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል።።



ሟች ንጉሴ አበበ

6. **ሟች ህጻን ዳንኤል ካሳ፡-** ዕድሜ 9፣ የ3ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 5፡00 ላይ ቆቦ ከተማ መናኸሪያ መግቢያ በር ላይ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ጀርባው ላይ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። በእለቱ ጥር 17 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ቆቦ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል።




ሟች ህጻን ዳንኤል ካሳ

7. **ሟች ሰይድ ፍሬው ፡-** ዕድሜ 31፣ ስራ ነጋዴ የነበረ ሲሆን ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 4:00 ላይ መርሳ ከተማ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ልቡ ላይ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ በእለቱ ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 ሰዓት ላይ መርሳ ከተማ ፊኛሮ ጥቁር አምባ የሙስሊሞች መቃብር የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ሟች በጤና ጣቢያው እርዳታ እየተሰጠው ሕወቱ ማለፉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ሟች ሰይድ ፍሬው

8. **ሟች መሀመድ አሰፋ፡-** ዕድሜ 18፣ የ10ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ሲሆን የካቲት 04 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 5:00 ላይ ውርጌሳ ከተማ ቴሌ ፊትለፊት በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ጭንቅላቱ ላይ በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ በእለቱ የካቲት 04 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ውርጌሳ ከተማ ገነት ማርያም ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና የአይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል፡፡



ሟች መሀመድ አሰፋ

9. **ሟች ምስጋናው ይመር፡-** ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም ከቤቱ የሞባይል ካርድ ለመግዛት እንደወጣ በመርሳ ከተማ ውስጥ በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል ፡፡ የቀብር ስነ-ስርዓቱም በነጋታው ጥር 20 ቀን 2010 ዓ.ም በ7 ሰዓት በቁትር ዘጠኝ ኩብያሎ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል ሲሉ የሟች ቤተሰቦችና በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ መርማሪዎች አስረድተዋል፡፡

10. **ሟች ጋሻው አወቀ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁከት ሕይወቱ ዓ.ም ማለፉን ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

11. **ሟች ናትናኤል መና፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁከት ሕይወቱ ማለፉን ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

12. **ሟች ሻምበል ፍትህ ርስት ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁከት ሕይወቱ ማለፉን ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

13. **ሟች አሸናፊ ሀይሉ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁከት ሕይወቱ ማለፉን ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ሟች አሸናፊ ሃይሉ ጥር 12 ወልደያ ከተማ የተገደለ መሞቱን ሆስፒታል አረጋግጧል

14. **ሟች ሞላ ብርሃኑ፡-** ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ ውስጥ በመንግስት የታጠቁ ሃይሎች በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ሟች በጤና ጣቢያው እርዳታ እየተሰጠው ሕይወቱ ማለፉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

15. **ሟች መካን አያሌው፡-** ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ በተካሄደበት እለት በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ ጉዳት እንደደረሰበትና በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኋላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ

ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቆየት ብሎ በደረሰን መረጃ መሰረት ጥር 22 ቀን 2010 ዓ.ም ደሴ ሆስፒታል በህክምና ላይ እንዳለ ሕይወቱ አልፏል፡፡

16. **ሟች ልዑል ፍስሀ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማ ውስጥ በተፈጠረው ሁከት ሚካኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ወደ ተከራየው ቤት በመግባት ላይ እንዳለ በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የሰመጉ ባለሙያዎች ያነጋገሯቸው የአይን ምስክሮች ገልጸዋል፡፡

17. **ሟች ተስፋዬ ሰጠኝ፡-** ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ በተካሄደበት እለት በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ ጉዳት እንደደረሰበትና በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኋላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቆየት ብሎ በደረሰን መረጃ መሰረት ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም ደሴ ሆስፒታል በህክምና ላይ እንዳለ ሕይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ተስፋየ ሰጠኝ ደሴ ሆስፒታል ገብቶ የሞተ

## 5.2 የአካል ጉዳት

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18(1) ‹‹ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢ- ሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው›› ተብሎ የተደነገገውንና በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ‹‹ማንም ሰው የማሠቃየት ድርጊት ሊፈጸምበት ወይም በጭካኔና ኢ ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ሊጉላላ ወይም ሊዋረድ አይችልም ወይም ሊቀጣ አይችልም›› እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 5 እና 6 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብር ያለው በመሆኑ ያላግባብ እንደማይታሰር፣ እንግልትና የማሰቃየት ድርጊት እንዳይፈፀምበት ይከለክላል፡፡ ኢትዮጵያ ተቀብላ የፈረመችው ማሰቃየትን፣ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ስብዓዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት በተደረገው ስምምነት ክፍል አንድ አንቀፅ 2 እያንዳንዱ ይህንን ስምምነት የተቀበለ ሀገር በግዛት ክልሉ ውስጥ በዜጎቹ ላይ በማናቸውም ሁኔታ የማሰቃየት ድርጊት መፈፀም እንደሌለበትና ይህንንም መከላከል እንዳለበት ስምምነቱን በፈረሙ ሀገራት ላይ ግዴታ ይጥላል፡፡ ተደንግጓል፡፡ እነዚህን ስምምነቶችና በህግ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱት ሰዎች ላይ በጥይት የማቁሰል ተግባር ተፈጽሟል፡፡

1. **ዳዊት ጥበቡ፡-** እድሜ 19፣ ጾታ ወንድ፣ ስራ ሹፌር፣ የመርሳ ወረዳ ነዋሪ ሲሆን ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም መርሳ ከተማ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የቀኝ ጉልበቱ ላይ በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ መርሳ ጤና ጣቢያ ገብቶ ሲታከም ከቆየ በኋላ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ሪፈር ተልኮ በህክምና ላይ እንደሚገኝ በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ ባሙያዎች አስረድቷል፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው በጤና ጣቢያው የመጀመሪያ እርዳታ ተደርጎለት ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና መላኩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡


ዳዊት ጥበቡ

2. **ዋሲሁን ታደሰ፡-** እድሜ 20፣ ጾታ ወንድ፣ ስራ ተማሪ፣ የሐብሩ ወረዳ ነዋሪ ሲሆን ጥር 20 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ላይ ወደቤቱ በመሄድ ላይ እንዳለ መርሳ ከተማ ወንዝ ላይ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ግራ እጁን በጥይት ተመትቶ መርሳ ጤና ጣቢያ ገብቶ ሲታከም ከቆየ በኋላ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ሪፈር ተልኮ በህክምና ላይ እንደሚገኝ በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ ባሙያዎች አስረድቷል፡፡


ዋሲሁን ታደሰ

3. **ቴዎድሮስ አበራ፡-** እድሜ 28፣ ጾታ ወንድ፣ የመርሳ ወረዳ ነዋሪ ሲሆን ጥር 19 ቀን 2010 ዓ.ም መርሳ ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ በተካሄደበት እለት ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ ከቤቱ በመውጣት ላይ እንዳለ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች ግራ እግሩ ላይ በጥይት ተመትቶ መርሳ ጤና ጣቢያ ገብቶ ሲታከም ከቆየ በኋላ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ሪፈር ተልኮ በህክምና ላይ እንደሚገኝ በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ ባሙያዎች አስረድቷል፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው በጤና ጣቢያው የመጀመሪያ እርዳታ ተደርጎለት ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና መላኩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡


ቴዎድሮስ አበራ

4. **ሙሉአለም ፍቅሬ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኂላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5. **ጀማል መሃመድ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኂላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

6. **ብርሃኑ ሰጠኝ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኂላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡


ብርሃኑ ሰጠኝ

7. **ኤፍሬም ታደሰ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በመርሳ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በመርሳ ጤና ጣቢያ የህክምና እርዳታ ከተደረገለት በኂላ ወደ ደሴ ሆስፒታል ለሪፈራል ህክምና እንደተላከ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ በሀብሩ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የመርሳ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የካቲት 09 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ/ጤ/ጣ/1507/2010 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

8. **ጋሹ ምትኬ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት እንደደረሰበትና በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና


እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

9. **ታደሰ ፈንታው ወልዴ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

10. **ዊንታና እሸቱ ታደሰ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትታ የአካል ጉዳት ደርሶባት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገላት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

11. **ብርቱካን መንግስቴ ፈንታው፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትታ የአካል ጉዳት ደርሶባት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገላት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

12. **ሞገስ አዲኖ አበበ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ሞገስ አዲኖ አበበ

13. **ሙሉቀን አባተ አስረስ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

14. **መላኩ ብርሃን አመሸ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

15. **ውብሸት አዲኖ ሞላ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

16. **ፍጹም አሰፋ ደሳለ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

17. **ተፈራ (የአባቱ ስም ያልታወቀ) ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት እንደደረሰበትና በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

18. **ሳሙኤል አምላኩ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

19. **ታምራት ማርዬ አስረስ፡-** ጥር 12 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች በጥይት ተመትቶ የአካል ጉዳት ደርሶበት በወልዲያ ሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ህክምና እንደተደረገለት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የወልድያ ጠቅላላ ሆስፒታል የካቲት 07 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ወ/ጠ/ሆ/3940/10 ዓ.ም ለሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ ማስረጃነት መሰረት ተጎጂው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

20. **ወ/ሪት ትዕግስት ተስፌ፡-** በወልድያ መምህራን ኮሌጅ ተማሪ ስትሆን ጥር 14 ቀን 2010 ዓ.ም በወልድያ ከተማ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች የቀን እጇና ኩላሊቷ ላይ በጥይት ተመትታ ወልዲያ ሆስፒታል ገብታ ስትታከም ከቆየች በኋላ ወደ ደብረታቦር ሆስፒታል ለሪፈር ተልካ በህክምና ላይ እንደምትገኝ ቤተሰቦቿ በአካባቢው ለተገኙ የሰመጉ ባሙያዎች አስረድተዋል፡፡


ወ/ሪት ትግስት ተስፌ

**ሰንጠረዥ 1** በወልድያ ከተማ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በተነሳው ሁከት ምክንያት በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጉዳቱ የደረሰበት ቦታ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | አድኖ ፈንታሁን | ሮቢት | 16/05/2010 |
| 2 | በላይ ደላለ | ›› | ›› |
| 3 | ተስፉ መለሰ | ›› | ›› |
| 4 | ክንድዬ መዝገቡ | ወልዲያ | 14/05/2010 |
| 5 | ጥላሁን ጌትነት | ›› | ›› |

## 6. ማጠቃለያ

በዚህ መግለጫ መግቢያ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ የተካተቱት የሞት፣ የአካል ጉዳት፣ የእሥራት፣ የደረሱበት የማይታወቁና ሌሎች ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈጸሙትን እና ሰመጉ በውስን አቅሙ ለማጣራት የቻለውን ብቻ ነው፡፡ በዚህ መግለጫ ውስጥ የተካተቱት የሞትና የአካል ጉዳት ማስረጃዎች በአብዛኛው የተገኙት ከሆስፒታሎችና ከጤና ጣቢያዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ግን የሰመጉ መርማሪዎች ጥሰት በተፈጸመባቸው አካባቢዎች በመዘዋወር ከሟች እና ከተጎጂ ቤተሰቦችና ከአይን እማኞች ያገኛቸው ናቸው፡፡

የደረሱትን የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አስመልክቶ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤትንና የሰሜን ወሎ ዞን ፖሊስ መምሪያን በደብዳቤ ብንጠይቅም ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለጻቸው ሰመጉ መርማሪዎቹ ተንቀሳቅሰው ያሰባሰቡትን ማስረጃዎችን ብቻ ለማቅረብ ተገዷል፡፡

ስለሆነም የተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ተጎጂዎች እንዲሁም ለሰብዓዊ መብት መከበር የምትቆረቆሩ ዜጎች ሁሉ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለሰመጉ እንዲደርስ በማድረግ የበኩላችሁን ድጋፍ በማድረግ የዜግነትና የሰብዓዊነት ግዴታችሁን እንድትወጡ ሰመጉ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 7. ማሳሰቢያ

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ተገቢ የሆነ ምላሽ መንግስት ባለመስጠቱ ምክንያት የተለያዩ ተቃውሞዎች በመቀሰቀሳቸውና በመነሳታቸው ለበርካታ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣ መቁሰል፣ መታሰርና ለከፍተኛ የንብረት መውደም ምክንያት ሆኗል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ /ሰመጉ/ ይህ ጉዳይ በቂ ትኩረትና ዘለቄታዊ ህጋዊ መፍትሄ እንዲሰጠው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

አሁንም በዚህ 145ኛ ልዩ መግለጫው መንግስት ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በቂ ትኩረት በመስጠትና በማዳመጥ፣ ለግጭቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑትን ምንጮች በማጥናት፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ እርምጃዎችን በመውሰድ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሀገራቸው በእኩልነትና በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲያመቻቹ ሰመጉ በዚህ መግለጫው ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም

- ሕገወጥ ግድያና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎችና ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣
- ለሰብዓዊ መብት ጥሰቶቹ ምክንያት የሆኑትን ችግሮችና ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመመካከርና በመወያየት የማያዳግም መፍትሄ እንዲሰጥ፣
- ከህግና ከዲሞክራሲ አግባብ ውጭ በዜጎች ህይወትና አካል ላይ ጥቃትና ጉዳት የፈፀሙና ያስፈጸሙ የመንግሥት አካላትን ለሕግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- መንግሥት ብሔርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገውን የፌዴራል አደረጃጀት ክፍተቶችና ችግሮች በመመርመር ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግ፣ በተለይም ዜጎች በማናቸውም የሀገሪቱ ክልል የመስራት፣ ንብረት የማፍራትና የመንቀሳቀስ መብታቸው እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ከክልላቸው ውጭ የሚኖሩ ዜጎች ተገቢ ጥበቃና ዋስትና እንዲያገኙ አስፈላጊውን ተቋማዊና ሕጋዊ ስርዓት እንዲዘረጋ፣
- የብሔር ተኮር ግጭቶችን የሚያነሳሱ ቅስቀሳዎችን በመከታተል ይህን በሚያደርጉ አካላት ላይ ፈጣን እርምጃ እንዲወስድ፤
- የቅርቡን ጊዜ ጨምሮ በሐገራችን የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነጻ፣ ገለልተኛና ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርቶ ችግሮችን በተጨባጭና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳየት እንዲሁም ኃላፊነት የተሞላበትና ገንቢ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ከሚረዱት መንገዶች አንደኛው ሐገር በቀል፤ አንጋፋና ነጻ የሆነውን የሰብዓዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔን - ሰመጉን በነጻነት፣ በስፋትና በሙሉ አቅሙ የሚሰራበትን የህግ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምህዳር ማስፋት ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ለሰመጉ ተገቢውን እውቅና፣ የመሥራት ነጻነት፣ ድጋፍና ጥበቃ እንዲያደርግለት፣
- በአጠቃላይ በተለያዩ ወቅቶች በሀገሪቱ የደረሰውን የህይወት፣ የአካልና የንብረት ጥፋት ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለማጣራት ጥያቄ ላቀረቡ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጽ/ቤት፣ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽንና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በጥያቄያቸው መሠረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ምርመራ ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና ስልክ በመደወል ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@ethionet.et፣

ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com
ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-
ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ
ስልክ ቁጥር +251 115541868
ፋክስ +25115517775
ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:
ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29
ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241
  ጂግጂጋ፣ ኢትዮጵያ
- ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ
- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499
  ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166
  አዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ
- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ
- ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 047 551-1544
ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ
- ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1799
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ
- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056
  ሰመራ ኢትዮጵያ
- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358
  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805
- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

**ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤**
**የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽ (FIDH) አባል፣**
**የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣**
**የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡**